# ህዳር ሲታጠን

ኅዳር የወር ስም ሆኖ በጥቅምት ወር እና በታኅሣሥ ወር መሀከል የሚገኝ ከአስራ ሦስቱ ኢትዮጵያ የወራት አቆጣጠር ውስጥ ሦስተኛው የወር ስም ነው።«ኅዳር» ከግዕዙ «ኀደረ» ከሚለው ግስ የተገኘ ነው።በዚህ ወር በምዕራባዉያን አቆጣጠር በ1918 ዓ.ም በአንደኛዉ የአለም ጦርነት መባቻ አካባቢ ከመካከለኛዉ ምስራቅ በድንገት ተነስቶ ቀስበቀስ ከቦታ ቦታ እየተላለፈ አለምን አዳርሶ ለ200 ሚሊዮን ሰዎች መጥፊያ መንስኤ የሆነዉ ስፓኒሽ ፍሉ ወይም የኢንፎሎዌንዛ የተባለዉ በሽታ ከላይ በተጠቀሰዉ ዓመተ ምህረት በህዳር ወር በኢትዮጵያ ግዛት ዉስጥ ተዳርሶ የህዳር በሽታ በሚል ስያሜ ስፍር ቁጥር የሌለዉ የሰዉ ህይወት አጥፍቷል። በዘመኑ የነበሩት ነገስታት በሽታዉ በቀላሉ ሊስፋፋ የሚችለዉ ከፅዳት ጉድለት መሆኑን ለህዝብ በአዋጅ ካስገነዘቡ በኋላ በየአካባቢዉ የሚገኙት ነዋሪዎች የመንደራቸዉን ቆሻሻ እያሰባሰቡ በማቃጠል በሽታዉን ለመከላከል ሙከራ አድርገዋል። ታዲያ ይህ የቆሻሻ ማቃጠል ልምድ በሽታ ለቆ ከሄደ በኋላ ከአመት ወደ አመት እየተስፋፋ ስለመጣ በየዓመቱ የህዳር ሚካኤል ክብረ በዓል ሲከበር ሰዎች እየተሰባሰቡ ህዳር ሲታጠን በሚል ዘመቻ በየቤታቸዉ አሮጌ እቃዎችን እና ቆሻሻ እያሰበሰቡ በማቃጠል በሽታዉ ያደረሰዉን ታላቅ ዕልቂት በየዓመቱ በህዳር ወር ማስታወስ እንደጀመሩ ታሪክ አዋቂዎች ይናገራሉ።

የበሽታው ምልክቶች ሳል፣ ከፍተኛ ትኩሳት፣ ነስር፣ የጆሮና የአንጀት መድማት፣ ተቅማጥ፣ የአይን ማስለቀስና ውጋት ሲሆኑ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሲደርስም የአእምሮ ህመም ያስከትላል።

በሽታው ከኮሌራ ወይም ከፈንጣጣ በሽታዎች ጋር ተቀራራቢ ምልክቶችን ስለሚያሳይ ብዙ ያምታታ ነበር። የበሽታው አስገራሚ ባህሪ፣ አንድ ሰው በበሽታው በተጠቃ በአምስት ቀን ውስጥ ወይ ይሞታል አልያም ከበሽታው ሙሉ ለሙሉ ይፈወሳል። ይህም እንደ ግለሰቡ የበሽታ መከላከል አቅም ይወሰናል፤ ቫይረሱ የተፈጥሮ የበሽታ የመከላከል አቅምን የሚያዳክም ሲሆን ጠንካራ የመከላከል አቅም ያለው ሰው ከአምስት ቀናት በላይ መቋቋም ስለሚያስችለው በስድስተኛው ቀን ፈውስ ያገኛል።

የበሽታው አማጪ ቫይረስ ባለመታወቁ መድሃኒትም ሆነ ማስታገሻ አልተገኘለትም። (እ.ኤ.አ በ1933 ዓ.ም በእንግሊዛዊያን ሳይንቲስቶች እንደተረጋገጠው የበሽታው አማጪ ቫይረስ በሳይንሳዊው አጠራር H1N1 ተብሎ ይታወቃል።

በኢትዮጵያ በሽታው የታየው የመጀመሪያው የበሽታው ምልክት በዓለም ላይ ከታየ ከአስር ወራት በኋላ በህዳር ወር 1911 ዓ.ም ነው። ከጥቂት ወራት ቀደም ብሎ በሽታው መግባቱ አይቀርም በሚል የቅድመ ጥንቃቄ ስራዎች መስራት እምብዛም የተለመደ አልነበረም። በዚህ

ረገድ ሊጠቀስ የሚችለው በኢትዮጵያ የኢጣሊያ ቆንሰላ ያደረገው ነገር ነበር። የታሪክ ምሁሩ ፕሮፌሰር ሪቻረድ ፓንክረስት እ.ኤ.አ በ1990 ዓ.ም ባሳተሙት An Introduction to the Medical History of Ethiopia በሚለው የምርምር ስራቸው ላይ እንደጻፉት፤ በሽታው በውል ያልታወቀ ነበርና ምናልባትም የፈንጣጣ በሽታ ይሆናል በሚል በወቅቱ በኢጣሊያ ቆንስላ ትብብር በሀምሌ ወር 1910 ዓ.ም አስር ሺህ ዶዝ የፈንጣጣ ክትባት ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ ተደርጎ ነበር። የሆነው ሆኖ ከዘመናዊ ህክምና ጋር ለማይተዋወቀው የኢትዮጵያ ህዝብም ወረርሽኙ ታላቅ መቅሰፍት ነበር። በሽታው ከቁጥጥር ውጭ ወጥቶ በመላው አገሪቱ ከባድ ዕልቂት ማስከተል ጀመረ። በተለይም ታላላቅ ኢትዮጵያዊያን በቫይረሱ መያዛቸውን ተከትሎ መረበሽን ፈጥሯል።

በበሽታው ከተጠቁ ታላላቅ የዘመኑ ሹመኞችና የቤተ መንግስት ሰዎች መካከል ራስ ተፈሪ መኮንን (ቀዳማዊ ሀይለ ስላሴ) እና ባለቤታቸው ወ/ሮ አቴጌ መነን አስፋው ይገኙበታል። እንዲያውም የራስ ተፈሪና ቤተሰቦቻቸው ሀኪም የሆኑት ሊባኖሳዊው ዶክተር አሳድ ቼይባን ራሳቸው የበሽታው ተጠቂ ነበሩና የራስ ተፈሪን ቤተሰብ የሚያክም ጠፍቶ እንደነበር የታሪክ ድርሳናት ያወሳሉ። ከህዳር 7 እስከ ህዳር 20 ቀን 1911 ዓ.ም ለአስራ አራት ቀናት ገደማ የቆየው በሽታው በህዳር ወር የተከሰተ በመሆኑም ህዝቡ የህዳር በሽታ እያለ ይጠራው ጀመር። ብላቴን ጌታ መርስዔ ሀዘን ወልደቂርቆስ የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በተሰኘው መጽሀፋቸው እንዳሰፈሩት፤ ወረርሽኙ እስከ አርባ ሺህ ኢትዮጵያዊንን ለሞት ዳርጓል፤ በአዲስ አበባ ከተማ ብቻ ዘጠኝ ሺህ ዜጎች በበሽታው ሞተዋል። በተለይም ህዳር 12 ቀን 1911 ዓ.ም በርካታ ኢትዮጵያዊያን የሞቱበት በመሆኑ በቀኑ የጽዳት ዘመቻ እንዲደረግ በአዋጅ ተነግሮ ስለነበር፣ ከዚያ በኋላ ባሉት ዓመታት ይህ ነገር እንደባህል ተወስዶ በየዓመቱ ህዳር 12 ቀን የጽዳት ዘመቻ ይደረግ ጀመር፤ ይህም በተለምዶ ህዳር ሲታጠን የምንለው ነው።ዶ/ር እናውጋው መሃሪ፣ዶ/ር ክንፈ ገበየሁ እና ዶ/ር ዘርጋባቸው አስፋው የተባሉ የህክምና ባለሙያዎች በጋራ ያሰናዱትና በ2013 እ.ኤ.አ የታተመው The Manual of Ethiopian Medical History ላይ እንደሰፈረው፤ የ1918ቱ የእንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ ክትባት ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው በአሜሪካን የቫንደርቢልት ዩኒቨርሲቲ (Vanderbilt University) ምሁራን ሲሆን ወቅቱም በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ነበር። ከዚያ በኋላ ባሉት ዘመናት በየጊዜው የተሻሻሉ ክትባቶች በምርምር ተገኝተዋል። በ1918 ዓ.ም እንደተከሰተው እንፍሉዌንዛ በወረርሽኝ መልክ ተከስቶ ባያውቅም ዛሬም ድረስ ግን የሰው ልጆች የጤና ፈተና መሆኑን አላቆመም። እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም ብቻ በመላው ዓለም አምስት መቶ ሺህ ሰዎች በበሽታው ህይወታቸውን አጥተዋል።

በዘርፉ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት፤ የኢንፍሉዌንዛ ክትባቶች የዋጋ ውድነት መፍትሄ ካላገኘ፣ ህዝቡ ስለ በሽታው በቂ ግንዛቤ ካላገኘ፣ መንግስታት በሽታውን ለመከላከል ከፍ ያለ ትኩረት ካልሰጡ በኢንፍሉዌንዛ ምክንያት የሚከሰተውን ሞት መቀነስ አዳጋች ነው፡፡

ምንጭ ፡- አዲስ አድማስ ህዳር 15 ቀን 2008 ዓ.ም እና ምንጃር ሸንኮራ ኮሙኒኬሽን